# ይድረስ ለብርቱዋ

(ከከበቡሽ አየናቸው)
ጥር 1 ቀን 2001 ዓ.ም.

ይድረስ ለብረቱዋ የጀግኖች ጀግና፣
በዚያው ባለሽበት እንዴት ነሽ በዝና?
በጣም ይረብሻል የሚመጣው ዜና።

ያንን ክፉ ወሬ ከሰማሁ ጀምሮ፣
በጣም ብሦበታል መጥፎው የኔ ኑሮ፣
ተስፋየም መንምኗል ከአምናው ዘንድሮ፤
ሰው እንዴት ይዘልቃል አገር ተበድሮ።

ከታጋዮች ሁሉ አንቺ ተለይተሽ፣
ብርቱዬ ብርቱዋ የተባረክሽ ነሽ፤
ከኢትዮጵያ ሴቶች አንቺን የመረጠሽ፣
የሕዝባችን ብሦት በምጥ የወለደሽ፣
ብርቱዬ ብርቱዋ ከቶ እንዴት ሰነበትሽ!?

ብሦቱን ተካፍለሽ አንቺ እንደምታውቂው፣
ጤናሽ ተጠብቆ ነፃ እንድታወጪው፣
ከፍርደ - ገምድሎች እንድታላቅቂው፣
ሕዝቡ ለአንች ሕይዎት ያስባል፣ ይሳሳል፤
በሕይዎት መኖርሽን በጣም ይፈልጋል፤
"አደራ ሕይዎትሽን ጠብቂልን" ይላል።

ለሕዝብ በገባሽው የማይታጠፍ ቃል፣
ጤናሽን መጠበቅ ከአንች የጠበቃል።

ብርቱዬ ብርቃችን መተኪያ የሌለሽ፣
ከተዳከምሽብን በማን ትተኪያለሽ?
አንቺን የመሰለ በቃሉ የፀና፣
ከሴቱስ ከወንዱስ መች ይገኛልና፣

ብርቱዬ ልንገርሽ በማይታበል ቃል፣
መጥፎ መጥፎ ወሬ ጠዋት ማታ ይፈልቃል፣
የአንቺ ምግብ መተው በጣም ያሰቅቃል፣
ምን እንደሚሰማኝ ባለቤቱ ያውቃል።

በእነርሱ ጭካኔ ፍትኅ - አልባነት ስንፈርድ፣
አንቺ እንዴት ትገቢ ባጠመዱት ወጥመድ?
ብርቱዬ ዳኛ ነሽ በጣም ሕግ አዋቂ፣
ነብስሽን - ሥጋሽን እንዴት ታስጨንቂ?

ቆራጥ መሆንሽን ዓለም አውቆልሻል፣
የሕግ አዋቂዎች ተሟግተውልሻል፣
ራስሽን ማጥፋቱ ያስፈርድብሻል፣
ግድያስ መሆኑ እንዴት ይጠፋሻል?

የትግል ጓዶችሽ ሳያወላውሉ፣
የብርቱካን ቃሏ ቃላችን ነው አሉ፤
ሕዝብም ተማፀኑ እንዳይደክም ትግሉ።

ብርቱዬ ብታይው በየኢንተርኔቱ፣
ሁሉም ከአንቺ ጋር ነው ይጎርፋል መልዕክቱ።

ለአንቺ ለቆራጧ ምኑ ይነገራል፣
እንዳለፈው ሁሉ ያሁኑም ቀን ያልፋል፣

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ለእኔ እንደሚታየኝ ከመቼውም ያጥራል።
ብርቱዬ ልንገርሽ ያላዘነ የለም፣
ምክሬን ተቀበይኝ ስሚኝ እህታለም።
እህቴ በእናትሽ ስለ ሀሌም ብለሽ፣
ስለገባሽው ቃል ስለሕዝቡም ብለሽ፣
ጠላት ደስ አይበለው ትንሽ ምግብ ቅመሽ፤
ለረጅሙ ጉዞ አምላክ ያጠንክርሽ!
ፍፁም ፀሎቴ ነው እንዲሳካ ህልምሽ፣
ሁሉ እማይሳነው አንድየ ፈጣሪሽ፣
ብርሃነ ጥምቀቱ በሩን ይክፈትልሽ፤
ፍትን የሰፈነባት ኢትዮጵያን ያሳይሽ።

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com